# የወቅቱ የአገሪቱ ችግር ሊፈታ የሚችል ነው

ኢብሳ ነመራ 12-26-17

አሁን በኢትዮጵያ ያለው ድባብ ከባድ ይመስላል። ይህ የሚከብድ ድባብ የተፈጠረው በተለያዩ የሃገሪቱ አካባቢዎች በተፈጠሩ ለሰው ህይወት መጥፋት ምክንያት በሆኑ ተከታታይ ግጭቶች ሳቢያ ነው። በተለይ ከ2009 ዓ/ም መጀመሪያ አንስቶ ሲካሄድ የቆየው በኦሮሚያና በኢትዮጵያ ሱማሌ አዋሳኝ አካባቢ የተቀሰቀሰ ግጭት ቀዳሚው ምክንያት ነው። ይህ ግጭት በራሱ ለበርካታ ዜጎች ህይወት መጥፋትና በመቶ ሺሆች ለሚቆጠሩ መፈናቀል ምክንያት ከመሆኑ በተጨማሪ ለሌሎች ጥያቄዎችና ችግሮችም መንስኤ ሆኗል።

በተደጋጋሚ ሲነገር እንደቆየው፣ በሁለቱ ክልሎች አዋሳኝ አካባቢዎች የተፈጠረው አለመግባባትና ግጭት መንስኤ በህዝበ ውሳኔ የተረጋገጠ ወሰን መሬት ላይ ሳይካለል መቆየት ነው። አለመግባባቱንና ግጭቱን የጫረው ይህ የወሰን አለመካለል ነው ቢባልም፣ ግጭቱ ግን አዋሳኝ አካባቢዎች በሚኖሩ የሁለቱ ክልሎች ብሄሮች ጉሳዎች መሃከል የተካሄደ ነው ማለት አይቻልም። የሁለቱ ክልሎች አዋሳኝ አካባቢዎች ነዋሪዎች እንደሚናገሩት፣ እነርሱም ለግጭቱ ባዳዎች ናቸው። ግድያዎች የሚፈጸሙት የአካባቢው ነዋሪ ባልሆኑ፣ በተደራጁና የውጊያ መሳሪያ በታጠቁ ቡድኖች ነው። ይህ ችግር በየወቅቱ ያለማቋረጥ ለሰዎች ህይወት መጥፋት ምክንያት መሆኑና የፌደራል መንግስት ይህን በአፋጣኝ አስቁሞ ለችግሩ እልባት ማበጀት አለመቻሉ የችግሩ ሰለባ የሆነው ህዝብ በፌደራል መንግስቱና በሃገሪቱ ሰላም አስከባሪ ሃይል ላይ ያላቸው እምነት እንዲሸረሸር አድርጓል። የህዝቡ በፌደራል መንግስቱ ላይ እምነት ማጣት ችግሩ በወቅቱ መፍትሄ አለማግኘቱ ያስከተለው ችግር ነው።

የግጭቱ መዘዝ በዚህ አላቆመም። በተለይ ከጳጉሜን 2009 ዓ/ም ጀምሮ ግጭቱ ተባብሶ በሁለቱም ወገን በመቶ ሺህ ለሚቆጠሩ ሰዎች መፈናቀልና ቁጥራቸው እስካሁን በይፋ ለማይታወቅ ሰዎች ሞት ምክንያት መሆኑ፣ ጉዳዩ ከሁለቱ ክልሎችም አልፎ የቀረውን የኢትዮጵያ ህዝብም ግር አሰኝቷል። መንግስት ይህን ችግር ለዘለቄታው መፍታት፣ መፍታት ባይችል እንኳን ግጭቱን ማስቆም እንዴት ያቅተዋል?! የሚል ቁጭት ቀመስ ጥያቄ ጭሯል። በተለይ በኦሮሚያ ውስጥ የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች ጉዳዩን በጥያቄ መልክ አንስተው ትምህርት ለማቆም እንደምክንያት አቅርበውታል። እውነቱን ለመናገር ይህ ጉዳይ በኦሮሚያ

ክልላዊ መንግስትና በፌደራል መንግስት መሃከል፣ እንዲሁም በኢህአዴግ ድርጅቶች መሃከል የተለመደው ተናቦ መንቀሳቀስ እንዲደፈርስ ምክንያት ሆኗል።

ከዚህ በተጨማሪ እዚያም እዚህም የግለሰቦችን ግጭትና መሰል ተልካሻ ምክንያቶች በስውር እጅ ወደ ብሄር ግጭትነት እንዲቀየሩ የተደረገበት ሁኔታ አለ። ይህ የየአካባቢው ጥቃቅን ግጭት በኦሮሚያና በኢትዮጵያ ሱማሌ ክልሎች መሃከል ከተፈጠረው ሰፋ ያለ ግጭት ጋር ተዳምሮ ሃገሪቱን የተተራመሰችና መንግስት ሃገሪቱን መምራት ያቃተው የሚያስመስሉ ሁኔታዎች ፈጥሯል። የሚከብድ ድባብ ያልኩት ይህንን ነው።

እነዚህ ሁኔታዎች ሳይመች ሰላማዊ የምርጫ ሂደትን፣ አመቺ ሲመስላቸው ደግሞ ሃይልን ጨምሮ ማንኛውንም ወደስልጣን ያደርሳል ብለው ያሰቡትን አቅጣጫ የሚከተሉ የፖለቲካ ፓርቲዎችና በውጭ ሃገር ህገመንግስታዊ ሥርአቱን ለማፈረስ መልካም አጋጣሚዎችን በመጠባበቅ ላይ የሚገኙ ቡድኖችን ከተኙበት ቀስቅሷል።

ሰሞኑን ሰላማዊ የፖለቲካ እንቅስቀሴ ለማድረግ ህጋዊ እውቅና የተሰጣቸው ሰማያዊ ፓርቲና የመላው ኢትዮጵያውያን አንድነት ድርጅት (መኢአድ) በውጭ ሃገር ከሚኖር ወደስልጣን መሹለኪያ ቀዳዳ ያለ ሲመሰለው ብቻ ድምጹን ከሚያሰማ *የኢትዮጵያ ህዝብ የጋራ ትግል ሸንጎ* ከተሰኘ ቡድን ጋር በጋራ ለመስራት መስማማታቸውን ሰምተናል። በጋራ ለመታገል የተስማሙት ጊዜው አመቺ ሰለሆነ ከምርጫ ውጭ ወደስልጣን የሚመጡበት እድል የተገኘ ስለመሰላቸው ይህ እንዳያመልጣቸው ነው። በጋራ ለመታገል መስማማታቸው ምንም ችግር የለውም።

በስልጣን ላይ ያለው መንግስት በሌላ መተካት አለበት በሚል የያዙትም አቋም በራሱ ምንም ችግር የለውም። የስልጣን ሽግግሩ ከምርጫ ውጭ በሆነ መንገድ እንዲከናወን ያስቀመጡት ሃሳብ ግን ጤናማ አይደለም። ሌሎች በሃገር ውስጥ የሚንቀሳቀሱ ፓርቲዎችም እንዲሁ ለምሳሌ መደረክ *ከምርጫ ውጭ የስልጣን ሽግግር ይደረግ* የሚል አቋሙን ጮክ ብሎ ማሰማት ጀምሯል። በዚህ ጽሁፍ የሰማያዊ ፓርቲ፣ የመኢአድና ራሱን የጋራ ሽትግ ሸንጎ ብሎ የሚጠራ ሰሞነኛ ቡድን አቋምና አካሄድ ላይ አተኩራለሁ።

ለጋራ ትግል ተሰባሰብን ያሉት እነዚህ ፓርቲዎች ስልጣን ላይ ያለው መንግስት አብቅቶለታል ባዮች ናቸው። በተለያዩ የሃገሪቱ አካባቢዎች የተቀሰቀሱ ግጭቶችን ለዚህ አስረጂነት ይጠቅሳሉ። አሁን በስልጣን ላይ ያለው መንግስት የጎሳ ፖለቲካ ስለሚያራምድ ውጤት ማምጣት አይችልም፤ የአንድነት ሃይሎች

ተባብረው ድል ሊያመጡ ይችላሉ የሚል አቋም እንዳላቸውም ገልጸዋል። ይህን መንግስትን የመቀየር ፍላጎታቸውን ለማሳካት ህገመንግስታዊውን የምርጫ ሂደት ቦታ አልሰጡትም። *ለጋራ ትግል ውል ገብተናል* ካሉት አንዱ የሆነው የሰማያዊ ፓርቲ ሊቀመንበረ አቶ የሺ ዋስ አሰፋ በዚህ ጉዳይ ላይ በሰጡት አስተያየት፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ለውድድር የሚያበቃ ምርጫ ቦርድ፣ ሚዲያ፣ የፍትህ ሥርአት የመሳሰሉት ስለሌሉ ወደትግል ገብተናል ብለዋል። ወደስልጣን ለመምጣት የምርጫን አማራጭ እንደማይቀበሉ ያመለከቱት እነዚህ በጋራ እንታገላለን የሚሉ ቡድኖች፣ አሁን ያለውን መንግስት የሚያስወግዱበት መንገድ ላይ ግን ግልጽ አይደሉም። ሁሉም የተካተተበት ውይይት ይደረግ፣ የሽግግር መንግስት ይመስረት፣ ህገመንግስትም የቀረጽ የሚል የተደበላለቀ ነገር ነው የሚናገሩት።

የፖለቲካ ፓርቲዎቹን የጋራ ትግል የሚል ነገር ውስጥ የከተታቸው ከላይ የገለጽነው በተለይ ከ2008 ዓ/ም ጀምሮ ሃገሪቱ ውስጥ የተቀሰቀሰው ተቃውሞ፣ ሁከትና ግጭት ነው። እነዚህ ነባራዊ ሁኔታዎች መንግስት ያበቃለት መሆኑን ያመለክታሉ፤ ስለዚህ ከምርጫ ውጭ ወደስልጣን የምንመጣበትን ወይም ትንሽም ቢሆን የምንጋራበትን እድል እንድናገኝ ምንግስትን እንግፋው በሚል ስሜት ነው የተነሳሱት። እዚህ ጋር አንድ በግልጽ መታወቅ ያለበት ነገር፣ አቋማቸው መንግስትን ህገመንግስታዊ ባልሆነ መንገድ አስወግደው ስልጣን ላይ የሚወጡበትን ሁኔታ መሞከር ነው።

እርግጥ ነው፤ ኢትዮጵያ ውስጥ ሁከት በተፈጠረ ቁጥር መንግስት ሊፈርስ እየመሰላቸው ካንቀላፉበት እየተነሱ ስለስልጣን ድልድል የሚያወሩ ቡድኖችን ማዳመጥ አዲስ ነገር አይደለም። ከላይ የተጠቀሰው የእነሰማያዊ ፓርቲ ወሬም ከእነዚህ አንዱ ነው። እዚህ ላይ አሁን ስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ከምርጫ ውጭ ማስወገድ የግድ የሚል ነባራዊ ሁኔታ አለወይ? እርግጥ መንግስት ሃገሪቱን መምራት አቅቶታል ወይ? የሚሉት ጥያቄዎችን ማንሳት ተገቢ ነው።

በሃገሪቱ ውስጥ ስጋት የፈጠሩ የግጭት ችግሮች መኖራቸው እውነት ነው። መንግስት ለተቀሰቀሱት ግጭቶች ወቅታዊ ፖለቲካዊና ህጋዊ መፍትሄዎች ማበጀትም ላይ ክፍተት ታይቶበታል። እርግጥ መንግስት እነዚህ ክፍተቶች ያሉበት መሆኑን አውቋል። አሁን ባለው ተጨባጭ ሁኔታ ለችግሮቹ ወቅታዊውም ይሁን ዘላቂ መፍትሄ ማበጀት የሚችለው በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ነው። በስልጣን ላይ ያለውን መንግስት ከምርጫ ውጭ ከስልጣን ለማስወገድ በማሰብ የሚነዛ ውዥንብር፣ ከውጭ ሃይሎች ጋር በመሆን መንግስት ላይ ጫና ለማሳደር የሚደረግ እንቅስቃሴ ችግሩን በማወሳሰብ መፍትሄ የማበጀቱን እርምጃ ከማደነቃቀፍ የተለየ ምንም የሚያስገኘው ፋይዳ የለም። ግጭት ውስጥ የገቡት ሁለቱም ብሄራዊ

ክልላዊ መንግስታት በኢፌዴሪ ህገመንግስት ላይ የማይናወጥ እምነት ያላቸው መሆኑን ማስታወስ ተገቢ ነው። ህገመንግስታዊ ስርአቱን የሚገፉ ማንኛውንም እርምጃ አይቀበሉም። ህገመንግስታዊውን ስርአት የሚፈታተን የከፋ አደጋ የመጣ ከመሰላቸው ተነጥለው የየራሳቸውን ክልል ማስተዳዳር ወደሚያስችላቸው እርምጃ ከማምራት የማይመለሱ መሆኑም መታወቅ አለበት። ይህ ደግሞ የሃገሪቱን አንድነት አደጋ ላይ የሚጥል ነው።

በዚህ ሁኔታ እነሰማያዊ ፓርቲ የሚያስቡት መንግስትን ገፍቶ የማስወገድ ህልም ቢሳካ ችግሩ ማንም ሊይዘው የማይችለው ውል አልባ ሆኖ ሃገሪቱን ሊበታትናት ወደሚችልበት ደረጃ መሸጋገሩ አይቀሬ ነው። እነሰማያዊ ፓርቲ ማስታወስ ያለባቸው የሃገሪቱ የመንግስት ስልጣን ያለው አዲስ አበባ ቤተመንግስት ሳይሆን ዘጠኙ ክልላዊ መንግስታት ጋር መሆኑን ነው። በሃይል አራት ኪሎ ቤተ መንግስት ቢገቡ፣ ሊጨብጧቸው የማይችሏቸው ዘጠኝ ትንንሽ መንግስታት እንዲፈጠሩ ከማድረግ ያለፈ የሚያተርፉት ነገር የለም። እርግጥ አሁን በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ችግሮቹን እንዳይፈታ ያደረጉትን ድክመቶቹን በይፋ ለህዝብ አሳውቆ፣ ችግሩን በተጨባጭ ሊፈታ የሚችል መፍትሄ በማቀረብ ከሁለት ዓመት ተኩል በኋላ በሚካሄደው ሃገራዊ ምርጫ ላይ በመወዳደር በዘጠኙም ብሄራዊ ክልላዊ መንግስት ለስልጣን የሚያበቃ ውክልና በማግኘት ወደስልጣን መምጣት ይቻላል። እነሰማያዊ ፓርቲ ግን  ይህን አማራጭ ይፈሩታል።

በመሰረቱ ሰማያዊ ፓርቲና አጋሮቹ ነን ባዮቹ አሁን በያዙት አቋም በሃገሪቱ ያጋጠሙ ችግሮችን መፍታት አይችሉም። ኢትዮጵያ ውስጥ የየራሳቸው ማንነት ያላቸው ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች የመኖራቸውን ግዙፍ እውነታ እንኳን መቀበል የማይፈልጉ ብሄሮችን ጎሳ በሚል ፍረጃ እንደ ተራ ነገር የሚያንቋሽሹ ሰማያዊ ፓርቲን የመሳሰሉ ቡድኖች አሁን ያለው የሃገሪቱ ነባራዊ ሁኔታ የፈጠራቸው አይደሉም። እነዚህ ቡድኖች የባለፉ አሃዳዊ ስርአቶች ቅሪቶች ናቸው። አንድ ስርአት ሲወገድ አመለካከቱ በቀላሉ ብን ብሎ አይጠፉም። በመቶ ለሚቆጠሩ ዓመታት የሚኖርበት ሁኔታ አለ። በአሜሪካ የባሪያ አሰዳሪ ሥርአት ካከተመ ሁለት ክፍለ ዘመን ያስቆጠረ ቢሆንም አሁንም የባሪያ አሳዳሪ አመለካከትን የሚያራምዱ ቡድኖች መኖራቸውን ልብ በሉ። ሰማያዊ ፓርቲና መሰሎቹ የዚህ አይነት ያረጀ አመለካካት ቅሪቶች ናቸው።

ያከተመላቸው ስርአቶች ቅሪት አመለካከቶች ህልውናቸው ሙልጭ ብሎ ባይጠፉም፣ የበላይ ሆኖ የመውጣት ምንም እድል የላቸውም። በአሜሪካ የባሪያ አሳዳሪ ሥርአት በምንም ምድራዊ ሁኔታ ሊመለስ አይችልም። መቼም ቢሆን ገዢ አመለካከት ሊሆን አይችልም። በሌላ አነጋገር ገዢ ፓርቲ የመሆን እድል ከቶም የለውም። እርግጥ ምክር ቤት ውስጥ በአንድ በሁለት መቀመጫዎች ውር ውር የሚልበት እድል

ሊኖር ይችላል። በኢትዮጵያ ሁኔታም ያለፉ ስርአት ቅሪት አመለካከቶች እጣ ፈንታ ከዚህ የተለየ አይደለም። አንድ ሁለት የምክር ቤት መቀመጫ ሊያገኙ የሚችሉበት እድል ሊኖር መቻሉ ግን አይካድም። በተለይ የፖለቲካ ፓርቲዎች ባደረጉት ድርድር እንዲስተካከል ሃሳብ ያቀረቡበት የአብላጫና ተመጣጣኝ ቅይጥ የምርጫ ሥርአት ህጋዊ ሆኖ ስራ ላይ ከዋለ የቀደሙት የአሃዳዊ ሥርአት አመለካከት አራማጆች አንድ ሁለት መቀመጫ ሊያገኙ የሚችልበት እድል ይኖራል። ከዚህ ግን አያልፉም።

እናም ሰማያዊ ፓርቲና አጋሮቹ አሁን በስልጣን ላይ ያለው መንግስት አብቅቶለታል ወይም ሃገሪቱን መምራት አልቻለም የሚለው አቋማቸው ትክክል እንኳን ቢሆን አሁን የተፈጠረው ችግር የመፍትሄ አካል እንኳን የመሆን ብቃት የላቸውም። የመንግስት ለውጥ፣ የሽግግር መንግስት፣ ህገመንግስት መቅረጽ ምንትስ ቅብጥርስ የሚለው ወሬያቸው የዋሆችን ከማደናገርና ምናልባት በውጭ ሃገር ከሚኖሩ የአሃዳዊ ስርአት ተስፈኛ ርዝራዦችን ቀልብ በመማረክ ዶላር መሰብሰብ ያስችላቸው እንደሆን እንጂ በተጨባጭ የሚያበረክተው ምንም አስተዋጽኦ የለውም።

በሌላ በኩል፣ በሃገሪቱ ችግሮች መኖራቸው ባይካድም አሁን በስልጣን ላይ ያለው መንግስት ሃገሪቱን መምራት ያቃተው ደረጃ ላይ አልደረሰም። እዚህም እዚያም ግጭቶች ቢኖሩም በሃገሪቱ አሁንም ህግና ስርአት የበላይነት አለው። እጅግ አብላጫ በሆኑ የሃገሪቱ አካባቢዎች ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ እንቅስቃሴዎች ቀደም ሲል በነበሩበት አኳኋን እንደቀጠሉ ነው። ያሀገሪቱ የውጭ ግንኙነትና ዓለም አቀፍ ተሳትፎ በነበረበት ሁኔታ እንደቀጠለ ነው። የቱሪስት ፍሰቱ፣ የውጭና የሃገር ውስጥ ኢንቨስትመንት በታቀደለት መሰረት እየተጓዘ ነው። የተጀመሩ ግዙፍ የልማት ፕሮጀክቶች የህዳሴውን ግድብ ጨምሮ ያለምንም መስተጓጎል እየተከናወኑ ነው። የሃገሪቱ አጠቃላይ የኢኮኖሚ እድገትም እንደቀጠለ ነው። አሁን ያለው ችግር በዚህ ዋና የሃገሪቱ መገለጫ ውስጥ አንድ ቦታ ላይ እንዳጋጠመ ቁስል የሚወሰድ ነው። የቆሰለ ሁሉ አይሞትም። እናም መንግስት ሃገሪቱን መምራት አላቃተውም፣ አላለቀለትም። ልዩ ትኩረት የሚጠይቁ ችግሮች ግን ገጥመውታል። እነዚህን ችግሮች ከህዝብ ጋር በመሆን የመፍታት እድል አለው። ይህን ማድረግ ካልቻለ ደግሞ ብቸኛ የመንግስት ስልጣን ምንጭና ባለቤት የሆነው ህዝብ በምርጫ ውክልናውን ነፍጎ ከስልጣን ያነሳዋል፤ በቃ። እውነታው ይሄው ነው።